# ለተማሪዎች የተዘጋጀ ሰነድ፣ ስለፊት ጭምብል መደረግ ያለባቸው እና መደረግ የሌለባቸው ነገሮች

የፊት ጭምብላችሁን በምታደርጉበትና በምታወልቁበት ወቅት ይህንን አድርጉ።

የፊት ጭምብላችሁን ከማድረጋችሁ በፊት እጆቻችሁን በሳሙናና ውሀ ታጠቡ ወይም የክፍል ውስጥ የእጅ ማጽጃ ተጠቀሙ።

የፊት ጭምብላችሁ በአፍና በአፍንጫችሁ ዙሪያ የሚገጥም መሆን አለበት።

የፊት ጭምብሉ ሽቦ ካለው ሽቦውን አፍንጫችሁ ላይ ቆንጠጥ በማድረግ ያስይዙ።

የፊት ጭምብላችሁን በምታደርጉበት ወቅት ላለመንካት መሞከራችሁ አስፈላጊ ነው። ጭምብሉን ማስተካከል ካለባችሁ፣ የጆሮ ማስገቢያዎቹን ተጠቀሙ ወይም ከጀርባው ለማሰር ሞክሩ።

ጭምብሉን በእጅ ከነካችሁት፣ እጆቻችሁን ታጠቡ ወይም የክፍል ውስጥ የእጅ ማጽጃ ተጠቀሙ።

ጭምብላችሁን በምታወልቁበት ጊዜ ፊት ለፊቱን አትያዙ። በጆሮዎቻችሁ ዙሪያ የሚዞሩትን የጆሮ ማስገቢያዎች ወይም በጭንቅላታችሁ ላይ የሚዞሩትን ማሰሪያዎች በመጠቀም ጭምብሉን አውልቁ።

ጭምብሎቻችሁን ካወለቃችሁ በኋላ፣ ወዲያውኑ እጆቻችሁን ታጠቡ ወይም የእጅ ማጽጃ ተጠቀሙ።

የእረፍት ጊዜ ወይም ምግብ መመገቢያ ጊዜ ስለመሳሰሉት ጭምብላችሁን ማውለቅ ስለምትችሉባቸው ጊዜያት አስተማሪዎቻችሁን ጠይቁ።

ጭምብላችሁን በማትጠቀሙበት ወቅት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለማስቀመጥ፣ ካወለቃችሁ በኋላ የት ማስቀመጥ እንዳለባችሁ ለማወቅ፣ አስተማሪዎቻችሁ የሚሰጡትን መመሪያ አድምጡ።

እና ደግሞ በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ንጹህ ጭምብል አድርጉ።

የእኔ ጭምብል እናንተን ይከላከላል፣ የእናንተ ጭምብል ደግሞ እኔን ይከላከላል።

ስለ COVID-19 ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት health.mn.gov የሚለውን ድረገጽ ተመልከቱ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

09/04/20
Mask Do's and Don'ts For Students (Amharic)
*ይህን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት ወደ 651-201-4989 ይደውሉ።*